

Source/ ፎቶው የተወሰደው ከ http://www.satenaw.com/wp-content/uploads/2016/10/mereja-53-satenaw-news.jpeg

# አማካሪው ማነው?

ብቅሉ ሲጠነሰስ ጌሾም እንዲጨመር፤
እነማን ነበሩ ጠላ ጠማቂወቹ
ዜጎች እንዲጠጡ በኢትዮጵያ አገር።
ቦታውስ የት ነበር የተማከሩበት፤
ጋኑንም በትንሽ ጠጠር የደጋገፉበት።

**በሰላም ሲሰለፍ ወጣት እንዲገደል**
**ወታደር ያዘዙ እጃቸውን አጥፈው፣**
**እነማን ነበሩ አማካሪስ ማነው?**
**እስኪ እንጠይቃቸው!**

አገሪ ኢትዮጵያ ምን መንግሥት አቋቋምሽ፤
በጥላው በርግጎ ላንቾ የቆሙትን የሚያሰቃይብሽ።
የዶሮ ብልቷ አሥራሁለት ነው
ተብሎ ስለሰሙ የህዋሃት ሞያተኞች፤
በጎሣ በለቱ የኢትዮጵያን ልጆች።
ዚገኖን አዘዘ ሁሉ እንዲበረግግ፣
እንዲህም አወጀ፣
አይንህ ብቻ ሳይሆን አዕምሮህን ዝጋ
በፍርሃት ማነቆ፣ እንዲያ ካለደረግህ፤
በአዋጅ ነግሪያለሁ አጋዚ አለብህ።

**በሰላም ሲሰለፍ ወጣት እንዲገደል**
**ወታደር ያዘዙ እጃቸውን አጥፈው፣**
**እነማን ነበሩ አማካሪስ ማነው?**
**እስኪ እንጠይቃቸው!**

አገሪ ኢትዮጵያ ምኑን መርዝ ጠጣሽው?
እርሃቡስ ቤበዛ ምኑን ምርዝ በላሽው?
ለቀብር ዳርጎሻል ከሆድሽ የወጣው።
እስኪ ሰላም ልበል ለኒያ ዘመዶቸ፤
ከአዲግራት፣ መቀሌ፣ ወልቃይት ጎንደር ውሥጥ
አርጎባ፣ ባሐር ዳር፣ አለፍ ብሎም ፍቼ።
ወደ ባሌም ልሂድ ሐረርንም ሳልተው አርሲም ሲዳማ፤
በረዲዮ ላስታውቅ ሁሉ እስኪሰማ።
ግልጽ አድርጌም ልንገር፤
የለቱን ግድያ በኢትዮጵያ እገር።

**በሰላም ሲሰለፍ ወጣት እንዲገደል**
**ፍትህ ለጠየቁት ጥይት ያበላቸው፣**
**ወታደር ያዘዙ እጃቸውን አጥፈው፣**
**እነማን ነበሩ፣ አማካሪስ ማነው?**
**እስኪ እንጠይቃቸው!**

አቤቱታ ላቅርብ ለራበው አባቴ፣
አቤቱታ ላቅርብ ለራባው ወንድሜ፣
አቤቱታም ላቅርብ ለራባት እህቴ፣
እንጀራ ብትሰጠኝ ያቾ ኢትዮጵያ እናቴ፤
ከታች ከላይ ስዞር ስቆም ለመብቴ።

© ለምለም ፀጋው፣October 17, 2016

በኢትዮጵያ ለምብታቸው ሲቆሙ ለተገደሉ ሁሉ መታሰቢያ